በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሐምሌ ፳ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

*የትምህርቱ ዓላማ* **በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ**

- ከወጣትነታችን ወራት ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር የመኖርን አስፈላጊነት መማር፡፡

*ጥቅስ*

- ‹‹በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡›› *መክ 12፡1፡፡*

*መግቢያ*

- ‹‹በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡›› *መክ 12፡1፡፡* የሚለው ኃይለ ቃል ‹‹ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም፡፡›› *ቀዳ ዮሐ 4፡10፡፡* እንዳለ ወጣቶችን በሚወደው በእግዚአብሔር የቀረበውን የፍቅር ጥሪ የሚያመለክት ነው፡፡
- የጥሪውም ዓላማ ለፍርድ ሳይሆን ደስታን ለማጎናጸፍ ነው፡፡ ‹‹ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፡፡›› *ዮሐ 7፡37፡፡* ብሎናልና፡፡ እኛም ለፍቅር ጥሪው ምላሽ መስጠት ይኖርብናል፡፡
- ምላሹንም በፈቃደኝነት መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ ምክንያቱም ከልጅነታችን ጀምሮ የወላጆቻችን ብቻ እንደሆን ስለሚሰማንና በዕድገታችንም የምናዳብራቸው ስሜቶች፣ ባሕሎች፣ አስተሳሰቦችና መርሆች ወደ ተለያየ አቅጣጫ ስለሚመሩን ነው፡፡
- ወጣቶች ዓለማዊ አቅጣጫን ተከትለው ቁሳዊ አስተሳሰብ እየመራቸው ‹‹ደስተኛ›› እንሁን በሚል ስሜት ሱሰኞች ሆነው በሕይወት ቢጓዙ ምን ይፈጠራል? ‹‹ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ይጠማልና›› የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ሳይሟላላቸው ሰላምን አጥተው ነፍሳቸው አስቀድመን የገለጽናቸው ጤናማ ባልሆኑ አካሄዶች ትጎዳለች፡፡
- *‹‹የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው፡፡ አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡›› **ገላ 5፡19-21፡፡***

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

- ወጣቶች ‹‹በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ።›› ያለውን የእግዚአብሔርን መንገድ ተከትለው ሲራመዱ ምን ይፈጠራል? ከዚህ ዓለም ኃጢአት ይሸሻሉ፣ በጥምቀት በተቀበሉት መንፈስ ቅዱስ ብዙ በረከቶች ይታደሉአቸዋል፣ ምሳሌ የሆነ አምላካችንንም መንገድ ተከትለው ‹‹ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።›› የተባሉትን የመንፈስ ፍሮዎች እያፈሩ ሲገዙ ይገኛሉ። *ገላ 5:22-23።*
- በሰው ልጆች ማንነት ውስጥ ዓለማዊ አቅጣጫንም ሆነ የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል በግልጽ ተለይተው ይታወቃሉ። ስለዚህ ወጣቶች የራሳቸውን ማንነትና ቅርጽ በእግዚአብሔር በማስተካከል የመንፈስ ቅዱስን በረከት ለመቀበል ዓለማዊ (ምድራዊ ከሆኑ ተራ ስሜቶች፣ አስተሳሰቦች፣ ጎጂ ባሕሎችና አጥፊ ከሆኑ የሕይወት መርሆዎች)) ከሆኑ ነገሮች ራሳቸውን ማራቅ ይጠበቅባቸዋል።

*ከሁሉ አስቀድሞ ስለ እግዚአብሔር ያለንን አስተሳሰብ እናስተካክል*

- በርካታ ሰዎች እግዚአብሔርን አለማመንን ስለምን መረጡ? ስለምንስ ከእግዚአብሔር ራቁ? ብዙዎችስ ስለምን ከእግዚአብሔር ጋር ክርክርን ይገጥማሉ? ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ዕውቀት የተሳሳተ ስለሆነ አይደለምን? ለእነርሱ እግዚአብሔር ተለይቶ በሰማይ ብቻ የሚኖር ፈጣሪና በዓለምም ላይ ሕግና ሥርዓትን በማውጣት ተጽእኖ የሚያሳድር አምላክ ነው።

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

- እንደነርሱ አመለካከት እግዚአብሔር የሰዎችንም ሥራ እየተመለከተ ከሚገጥማቸው ከፍርሐታቸው፣ ከምኞታቸውና ከፍላጎታቸው ርቆ ቆይቶ በኋላም የሚፈርድባቸው ነው፡፡
- ይህም በክርስናው እውነት ውስጥ የማናገኘው ስለእግዚአብሔር የተቀረጸባቸው የተሳሳተ ሥዕል ነው፡፡
- እውነታውም እግዚአብሔር ፍጥረታቱን የሚወድ ፈጣሪ መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡ በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡›› ***<u>ቀዳ ዮሐ 4፡8-9፡፡</u>*** ‹‹በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡›› ***<u>ዮሐ 1፡14፡፡</u>***
- ስለወደደንም ሥጋችንን ለብሶ ሰው በመሆን፣ የፍቅር - የርኅራኄና - የነፍሳችንን ፈቃድ ደስታዋን የተሟላ ያደርግ ዘንድ የአባትነት ግኑኙነትን ከእኛ ጋር መሠረተ፡፡
- ሰው በመሆኑ፣ በመስቀል ተሰቅሎ በመሞቱና በትንሣኤውም ንስሐ ገብተን በተቀበልነውና በምንቀበለው ሥጋውና ደሙ ያለፍርድ እንኖር ዘንድ አበቃን፡፡ ብንበድል እንኳ የንስሐና በደሙ ከኃጢአት የምንነጻበት በር አልተዘጋም፡፡

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

***በጉብዝና ወራት እግዚአብሔርን የመከተል አስፈላጊነት***

1. አንድ ባለብዙ ፎቅ ሕንጻ ጥሩ መሠረት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ወጣቶችም በመንፈሳዊ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ለማደግ በሕይወታቸው መንፈሳዊ መሠረት መጣልና በዚያም ላይ ማደግ ስለሚገባ፡፡
2. ከአምላካችን ከክርስቶስ ጋር የሆነ ሕይወት ሰላምና ደስታን የተሞላ ስለሆነ ይህንም በጉብዝናችን ወራት መቅመስ ስለሚያስችለን፡፡ ከአእምሮ በላይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሰላም ርቀን ሕይወታችንን ስለምን እያበላሸን ዘመናችንን እናጠፋለን?
3. እግዚአብሔር ወዶን ‹‹በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ›› ብሎ ከጠራን ለጥሪው ስለምን ምላሽ አንሰጥም? ለርሱስ ከሁሉ የተሻለውንና የጥንካሬውን ዘመናችንንስ ስለምን አንሰጥም? ‹‹ጕበዞች ሆይ፥ ብርቱዎች ስለ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስለ አሸነፋችሁ እጽፍላችኊለሁ፡፡›› *<u>ቀዳ ዮሐ 2፡14፡፡</u>*
4. እግዚአብሔርን ለረጅም ዘመናት በማገልገል በረከትን ለመቀበል፡፡ ወጣቶች በልጅነታቸው ከእግዚአብሔር ጋር ግኑኝነት ከመሠረቱ ልቦናቸው በእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላ ሆኖ ስለ እግዚአብሔርም ለሌሎች የሚያስረዱ ይሆናሉ፡፡
5. በልጅነታችን ግኑኝነቱን ከመሠረትን መንፈሳዊ ዕውቀታችንንና መንፈሳዊ ብስለታችን እያደገ ይሄዳል፡፡ ቅዳሴን በማስቀደስ፣ የቤተ ክርስቲያንን ዜማ በማጥናት፣ በጸሎት፣ ማኅሌቱንና ዝማሬውን በማጥናት፣ የቅዱሳንን ሕይወት፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናት፣ … ካደግን ዘላለማዊ ርስትን እስከመውረስ የሚያበቃ ዕድላችንን ያሳምራል፡፡
6. የድኅነትን ጎዳና፣ መንግስተ ሰማያትንም የመውረስን ነገር መረዳት ስለሚገባን፡፡ ይህም የመረዳት ፍለጋም ጊዜንና ቀጥተኛነትን በመንፈሳዊ ሕይወት ይሻሉ፡፡

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

***ወጣቶች በጉብዝናቸው ወራት ከእግዚአብሔር ጋር ሲሆኑ የሚገጥሟቸው መሰናክሎች***

1. ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፡፡›› ***ማቴዎስ 7፡13-14***፡ ያለውና
2. ዓለምና ያለምን እንቅፋት በርዋን ለወጣቶች ክፍት ማድረግዋ፡፡ ሁሉም ነገር ሙሉ ሁሉም ውብ ሆኖ ይታያቸዋል፡፡ ብዙዎችም ይህን የዓለምን መንገድ ተከትለው ይበላሻሉ ቀልጠውም ይቀራሉ፡፡ የእግዚአብሔር መንገድ አስቸጋሪ ቢመስልም ከአእምሮ በላይ በሆነ ሰላምና ዘላለማዊ ሕይወትን በመውረስ የሚጠናቀቅ ነው፡፡ ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ በራዕዩ የተመለከተውም ይህንኑ ነው፡፡

- ‹‹ከዚህ በኂላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፡፡ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ፡፡መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡፡አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ፡፡ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ፦ እነዚህ ነጨን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ፡፡እኔም፡፡ ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት፡፡ አለኝም፡፡ እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ፡፡›› ***ራእ 7፡9-14፡፡***
- መንገዱ ጠባብ ቢሆንም ከእኛ የሚፈለገው እግዚአብሔርን የመከተል ፈቃደኝነት እስከተገኘ ድረስ ይረዳናል ይደግፈናልና ወገኖቼ ሆይ ደስ ይበለን!!!

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

- ‹‹ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡›› *ፊል 4፡13፡፡*
- ‹‹ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት፥ ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ፡፡›› *ካል ጢሞ 4፡17፡፡*
- ‹‹ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?›› *ቀዳ ቆሮ 15፡55፡፡*
- ‹‹በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፥ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው፡፡›› *ኢሳ 63፡9፡፡*

*በወጣቶች ሕይወት እንቅፋት የሚሆኑት ነገሮች ምንድር ናቸው?*

1. መጽሐፍ ቅዱስንና ትርጓሜውንም በአግባቡ አለመረዳት፡፡
2. ለተወሰኑ ቅደም ተከተሎችና ሥርዓቶች ብቻ ተገዢ መሆን፡፡
3. ጥርጥርና ለሰይጣን ዕድል መስጠት፡፡
4. ታማኝ አለመሆን፡፡
5. ከሌሎች የሚመጣ ፈተና ወይም ምኞት፡፡
6. ሕይወትን በእግዚአብሔር አለመቅመስ፡፡
7. ትዕቢት፡፡

*በሚከተሉት የተነሳ በኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ሕይወት የንጽሕና ዕድል ሊገኝ ይችላል*

- ንጽሕና ክፉ ነገሮችን ሁሉ ማስወገድ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ መሆን ነውና፤ ሆነው መገኘት መቻል፡፡
- እግዚአብሔር በልባችን ማሳደር - ይህም ክፉ ሁሉ ከሕይወታችን ይርቅልናል፣ ይወገድልናል፡፡
- በበደልን ጊዜ አብዝተን ስለርሱ መጨነቅ ሳይሆን ቅዱስ ጴጥሮስን ከባሕር ስጥመት ያዳነውን አምላካችንን በማሰብ ንስሐ ገብተን ኃጢአታችንን በንስሐ መፋቅ፡፡

# በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ

- እግዚአብሔርን በወደድነው መጠን ዘወትር ወደርሱ መጸለይ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ትርጓሜያቸውን ማጥናት ይህን በማድረግ በቅድስና እንኖር ዘንድ ይቻለናልና፡፡
- እኛ ከኃጢአት ሁሉ የሚያነጻን በጸሎትም የሚቀድሰን የመንፈስቅዱስ ማደሪያዎች እንደሆንን መረዳት፡፡
- እግዚአብሔር በሕይወታችን ሲገኝ ‹‹እንዲህ ያለውን ስህተት በርሱ ፊት እንዴ እፈጽመዋለሁ›› ለማለት መቻል፡፡
- ክፉ ማየትን፣ ክፉ መናገርን፣ ክፉ ማሰብን ከውስጣችን እስካልመነጨ ድረስ መቃወም፡፡ ከውስጥ የመነጨውን መቃወም ግን ቢቸግረንም ለእግዚአብሔር አስልፈን እንስጠው እርሱም ያስተካክለናልና፡፡

***<u>በወጣትነታቸው እግዚአብሔርን በማሰብ የተገኙ ቅዱሳን</u>***

- ነቢዩ ዳንኤል፣ ሦስቱ ወጣቶች፣ ዮሴፍ፣ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር የሆነ ጢሞቴዎስ፣ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ፡፡

***<u>መፍትሔዎች</u>***

- ዘወትር ቢያንስ አንድ ምዕራፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ እናንብብ፡፡
- መንፈሳውያን የሆኑ መጻሕፍትን እናንብብ፡፡
- በተቻለን መጠን ወደ ቅዱሳት መካናት - ወደ ገዳማት በመሔድ ከመንፈሳውያን አባቶች ጸሎታቸውን/ቡራኬያቸውን ምክርን እንቀበል፡፡
- በግላችን፣ በቤተሰብም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ተግተን እንጸልይ፡፡
- ንስሐ በመግባት ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል እንጽና፡፡
- ዮሴፍ እንዳደረገው ኃጢአት ከሚደረግበት ቦታ እንሽሽ፡፡ *<u>ዘፍጥ 39፣ ቀዳ ቆሮ 6፡18፣ ካል ጢሞ 2፡22፡፡</u>*
- ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጠቃሚ ያልሆኑ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ከመመልከት እንቆጠብ፡፡
- ተሰጥኦአችንንና ችሎታችንን ለይተን በማወቅ ለተሰጠን ችሎታ ጥንቃቄ እናድርግ፡፡ *<u>ማቴ 25፡14-30፡፡</u>*
- በበደልን ጊዜ ሳንዘገይ ፈጥነን ንስሐ በመግባት በአምላካችን ሥጋና ደም (ቅዱስ ቁርባን) ከኃጢአታችን ታጥበን ወዳጅነታችንን አጽንተን እንኑር፡፡ *<u>ሉቃ 13፡1-5፡፡</u>*

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org